# ምስጢረ ክህነት።

## ክህነት ምንድን ነው?
ክህነት ለእግዚአብሔር የሚቀርብ የተቀደሰ አገልግሎት ነው።

## የክህነት አገልግሎት የተጀመረው በየት ነው?
የክህነት አገልግሎት የተጀመረው በላይ በሰማይ ነው። ኀያ አራቱ መላእክት (ካህናተ ሰማይ) የእግዚአብሔር አገልጋዮች ይባላሉ። የእግዚአብሔርን ቅዱስ መንበር የተሸከሙ አራቱ መላእክት (አራቱ እንስሳት) እና ኀያ አራቱ ካህናት እግዚአብሔርን ያለ ዕረፍት፣ <<ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ ቅዱስ፣ የነበረና ያለ የሚመጣው ኹሉንም የሚገዛ>> እያሉ ሲያመሰግኑ ይኖራሉ። እንደዚሁም ኀያ አራቱ ካህናት በእግዚአብሔር መንበር ዙሪያ እየሰገዱ፣ <<ጌታችንና አምላካችን ሆይ አንተ ኹሉን ፈጥረሃልና፣ በፈቃድኽም ሆነዋልና፣ ተፈጥረዋልምና ክብር ውዳሴ፣ ኀይልም ልትቀበል ይገባሃል>> እያሉ በመንበሩ ፊት እየሰገዱና አክሊሎቻቸውን እያኖሩ ያመሰግኖታል (ራእ 4፣ 8-11)።

## በምድር ላይ የመጀመሪያው የእግዚአብሔር ካህን ማን ነበረ?
በምድር ላይ የመጀመሪያው የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሳሌም (እየሩሳሌም) ንጉሥ የነበረው መልከ ጼዴቅ የተባለው ሰው ነው (ዘፍ 14፣ 18)።

## ካህንና ንጉስ የነበው መልከ ጼዴቅ የማን ምሳሌ ነበር?
በኋላ ዘመን በሥጋ ለተገለጠው ለማይሻረው ንጉሥና ለእውነተኛው ካህን ለክርስቶስ ምሳሌ እንደ ነበር መጻሕፍት ይመሰክራሉ። <<አንተ ካህኑ ለዓለም በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ>> ፤ <<አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ዘላለማዊ ካህን ነህ>> ተብሎ ለክርስቶስ ተነግሮለታል (መዝ.109(110)፣ 4)። ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም መልከ ጼዴቅ የእግዚአብሔር ካህንና የሰላም ንጉስ ተብሎ የተጠራው በኋላ ዘመን ሰው ኾኖ ለተገለጠው ለወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ምሳሌ መሆኑል አረጋግጦአል (ዕብ 6፣ 20፤7፣1-3)

## ኦሪት ከተሰጠች በኋላ የመጀመሪያው ካህን ማን ነበረ?
ኦሪት ከተሰጠች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ካህን ሆኖ የተሾመው አሮን ይባላል። አሮንንና የአሮንን ልጆች ካህናት አድርጎ የሾማቸው ካህንና መስፍን የነበረው ሙሴ ነው። ሙሴ በእግዚአብሔር ተመርጦ የተሾመ ካህን ነብይና መስፍን ስለ ነበር፣ በእግዚአብሄር ትእዛዝ አሮንንና ልጆቹን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ካህናት አድርጎ ሙሉ ልብሰ ተክህኖ (ልብሰ ክህነት) አልብሶ ሾማቸው (ኦሪት ዘጸአት ምዕራፍ 28 ና 29 ይመልከቱ)።

## የእግዚአብሔር ካህናት ሆነው የተሾሙ አሮንና ለጆቹ ምን ይሠሩ ነበር?
አሮንና ልጆቹ ሙሉ ልብሰ ክህነት (ልብሰ ተክህኖ) እየለበሱ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን አገልግሎት ይፈጽሙ ነበር፦

1ኛ) በደብተራ ኦሪት (በድንኳኑ) ውስጥ ልዩ ልዩ መንፈሳዊ ምስጋናን ለእግዚአብሔር ያቀርቡ ነበር፤

2ኛ) ስለ ራሳቸው ስለ ሕዝበ እስራኤል ኃጢአት የይቅርታ (የስርየት) መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር፤

3ኛ) ልዩ ልዩ መሥዋዕት ከማሳረጋቸው በላይ በማዕጠንት ወርቅ ለእግዚአብሔር የዕጣን መሥዋዕት ያቀርቡ ነበር፤

4ኛ) ቅብዐ ክህነት የተቀባው ሊቀ ካህናት ለመሥዋዕት ከታረደው እንስሳ ደም፣ በደብተራ ኦሪት ውስጥና በዙሪያው በመርጨት የሕዝቡን በደል ያስተስርይ ነበር (ዘሌዋ. 4፣ 1-35፤ ዕብ. 9፣ 15-26)፤

5ኛ) አርንና ልጆቹ ስለ ራሳቸውና ስለ ሕዝቡ፣ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት ያቀርቡ፣ ደምም ይረጩ ነበር (ዘሌዋ. 9፣ 1-14)፤

6ኛ) በሕግ የታዘዘውን መሥዋዕት (መባ) ከአራስ ቤት እየተቀበሉ ስርየት ያደርጉላት ነበር (ዘሌዋ.12) ከለምጻሙም በሕግ የታዘዘውን መባ እየተቀበሉ፣ ደዌውን ያስወግዱ ነበር (ዘሌዋ.13፤ 14)፤

7ኛ) በኦሪት በታዘዘው መሠረት በልዩ ልዩ ምክንያት ረክሰዋል ተብለው የተገመቱትን ወገኖች ካህናቱ የሚገባውን መሥዋዕት (መባ) ተቀብለው የተባረከውን ውኃ ይረጩበታል፣ እነርሱም ንጹሐን ይኾኑ ነበር (ዘህል. 19፣ 1-22)

8ኛ) አሮንና ልጆቹ የእስራኤልን ልጆች በእግዚአብሔር ስም እንደሚከተለው ይባርኳቸው ነበር <<እግዚአብሔር ይባርክህ ይጠብቅህ፣ እግዚአብሔር ፊቱን ያብራልህ ይራራልህም፣ እግዚአብሔር ፊቱን ወደ አንተ ይመልስ ሰላምን ይስጥህ>> (ዘህል. 6፣ 22)

የአሮንና የልጆቹ ክህነት ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመሠረተው አማናዊው ክህነት፣ ታሪካው ምሳሌ መሆኑን መገንዘብ ይገባል

## ክህነት በሐዲስ ኪዳን ዘመን

### እውነተኛውን (አማናዊውን) ክህነት የመሠረተ ማን ነው?

እውነተኛውን (አማናዊውን) ክህነት የመሠረተው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፣ <<ቅዱስ፣ ተንኮልና ነውር የሌለበት፣ ከኃጢአት የተለየ (ኃጢአት የሌለበት) ከሰማያት ከፍ ከፍ ያለ እውነተኛ ሊቀ ካህናት ነው>> (ዕብ.6፣ 26-28)።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱሳን ሐዋርያትን ተከታዮቹ (ደቀ መዛሙርቱ) እንዲሆኑ ከመረጣቸው በኋላ ሰፊ ስልጣን ሰጥቶአቸዋል፦

1ኛ) <<በምድር የምታስሩት ኹሉ በሰማይ የታሰረ ይኾናል፤ በምድር የምትፈቱት ኹሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል>> (ማቴ.18፣ 18)

2ኛ) <<መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ፤ ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኋቸውን ኹሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ኹሉ ይያዝባቸዋል፤ >>

3ኛ) <<ድውዮችን ፈውሱ፣ ሙታንን አንሡ፣ ለምጻሞችን አንጹ፣ አጋንንትን አውጡ>> (ማቴ.10፣ 1-2)፤

ቅዱሳን ሐዋርያትም ከጌታችን የተቀበሉትን ሥልጣነ ክህነት በአንብሮተ እድ (በራሳቸው ላይ እጅ በማኖር) ለተከታዮቻቸው አስተላልፈዋል። የቅዱሳን ሐዋርያት ተከታዮችም እንደዚሁ ተከታዮቻቸውን በአንብሮተ እድ ሾመዋል (የሐዋ.6፣ 2-6)።

በዚሁ በሐዋርያት ሥርዓት (ቀኖና) መሠረት፣ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ኤጲስ ቆጶሳትን፣ ቀሳውስትን ዲያቆናትን በአንብሮተ እድ ትሾማለች። የፓትሪያርክነትና የሊቀ ጵጵስና ሥልጣን ግን፣ ያለ አንብሮተ እድ በምርጫና በጸሎት ይሰጣል።

### በአንብሮተ እድ የሚሰጡ የክህነት ደረጃዎች ስንት ናቸው?

በአንብሮተ እድ (እጅ በመጫን) የሚሰጡ የሥልጣነ ክህነት ደረጃዎች ሦስት ናቸው።
እነርሱም፦

ሀ. ዲቁና፣
ለ. ቅስና፣
ሐ. ኤጲስ ቆጶስነት ናቸው

በአንብሮተ እድ የማይሰጡ ግን ከዲቁና በፊት የሚሰጡ የመንፈሳዊ አገልግሎት ሹመቶች አሉ፤ እነዚህም፣

ሀ. አጻዌ ኆኅት፣ ማለት በረኛ፤
ለ. አናጉንስጢስ፣ ማለት አንባቢ፤
ሐ. ንፍቀ ዲቁና፣ ማለት ተራዳኢነት፤
መ. መዘምርነት፣
ሠ. ዲያቆናዊት፣ (ሴት ስትጠመቅ የምትረዳ የሴት ዲያቆን)።

## ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሹመቶች መስጠት (መሾም) የሚችል ማን ነው?

የዲቁና፣ የቅስና፣ የአጻዌ ኆኅትነት፣ የአናጉንስጢስነት፣ የንፍቀ ዲቁናን ሥልጣል መስጠት የሚችል ኤጲስ ቆጶሳት ናቸው።

## ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው በማን ነው?

ኤጲስ ቆጶስ የሚሾመው በቅዱስ ፓትርያርኩና በሊቃነ ጳጳሳት ቡራኬ ነው።

## የአናጉንስጢስ ሥራ (አገልግሎት) ምንድር ነው?

አናጉንስጢስ ቃሉ ዕርዕ ሲሆን፣ ትርጉሙ አንባቢ ማለት ነው። ሥራውም በቤተክርስቲያን ውስጥ ቅዱሳት መጻሕፍትን አጣርቶና አሰምቶ ማንበብ ነው።

## የመዘመር አገልግሎት ምንድር ነው?

የመዘመር አገልግሎት፣ በአገልግሎት ጊዜ መንፈሳዊ መዝሙርችን መዘመር ነው።

## የአጻዌ ኆኅት አገልግሎት ምንድን ነው?

የአጻዌ ኆኅት አገልግሎት የቤተ ክርስቲያንን በር መጠበቅ በሩን መክፈትና መዝጋት አገልግሎት በሚሰጥበትና በሌላም ጊዜ ምዕመናንን ለማስቸገር፣ ሰላምን ለመንሳት፣ ጸጥታን ለማወክ የሚመጡትን ኹሉ መከልከል ነው

## የንፍቀ ዲያቆን አግልግሎት ምንድን ነው? ለመንፈሳዊ አግልግሎት

የንፍቀ ዲያቆን አግልግሎት ለመንፈሳዊ አግልግሎት የሚላኩትን ካህናትና ዲያቆናቱን መርዳት ነው።

## የዲያቆናዊት አገልግሎት ምንድን ነው?

ስለ ዲያቆናዊት ሴቶች አገልግሎት፣ በዲድስቅልያ አንቀጽ 17 ላይ ተወስኖአል። እርሱም ቀጥሎ ያለው ነው፤ <<ኤጲስ ቆጶስ ንጹሖችን ሴቶች መርጦ ሴቶችን ለማገልገል ዲቁናን የሾማቸዋል። ምዕመናት ሴቶችን ለሚያስፈልጋቸው ነገር በጠሩ ጊዜ፣ ከዲያቆናዊት በቀር ወንድ ዲያቆን ወደ ሴቶች ቤት ሊልክ አይገባውም። ስለዚህና ስለሚያጠምቋትም ሴት ሰውነትዋን ሚርን ትቀባ ዘንድ ነው። ወንድ የተራቆተችውን ሴት ማየት አይገባውምና።>>

## ሥልጣነ ክህነት በአንብሮተ እድ መስጠት ወይም መሾም ማለት እንዴት ነው?

ፓትርያርኩና ሊቃነ ጳጳሳቱ በንጽሕናውና በትምህርት ችሎታው ተመርጦ የቀረበውን ቆሞስ መነኩስ እጃቸውን በራሱ ላይ በማኖር በጸሎት ኤጲስ ቆጶስ ብለው ይሾሙታል። ኤጲስ ቆጶሱም እንዲሁ ለዲቁና፣ ለቅስና ሥልጣን የሚያበቃ ትምህርት ተምረውና ተመርጠው የቀረቡትን እጁን በራሳቸው ላይ በማኖር ዲያቆን፣ ቄስ ብሎ ይሾማቸዋል።

በአንብሮተ እድ ማለት እጅ በመጫን ሥልጣን በመስጠትና ተከታዮችን መሾም በዘመነ ኦሪትም የተለመደ ሥርዓት እንደ ነበር ቅዱስ መጽሐፍ ይመሰክራል። ይኸውም በሙሴና በኢያሱ ታውቆአል። ሙሴ በዕድሜ እየሸመገለና ጉልበቱም እየደከመ በሄደ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር እንዲህ ሲል አመለከተ፤ <<የእግዚአብሔር ማኅበር እረኛ እንደሌለው መንጋ እንዳይሆን፣ በፊታቸው የሚወጣውን፣ በፊታቸው የሚገባውን የሚያስወጣቸውና የሚያስፈልጋቸውን ሰው፣ የሥጋ ኹሉ መንፈስ እግዚአብሔር በማኅበሩ ላይ ይሹመው>> (ዘሁል.27፣ 15-18)።

እግዚአብሔር የሙሴን ጸሎት ሰምቶ እንዲህ ሲል አዘዘው፤ <<መንፈስ (መንፈስ ቅዱስ) ያለበትን ሰው፣ የነዌን ልጅ ኢያሱን ወስደህ እጅህን በላዩ ጫንበት፤ በካህኑ በአልዓዛርና በማኅበሩ ኹሉ ፊት አቁመው እነርሱም እያዩ እዘዘው። የእስራኤልም ልጆች፣ ማኅበሩ ኹሉ እንዲታዘዙለት ከክብርህ (ከሥልጣንህ) አኑርበት። በካህኑም በአልዓዛር ፊት ይቁም፤ እርሱም

(ካህኑ) በእግዚአብሔር ፊት በኡሪም ፍርድ ይጠይቅለት፤ እርሱና ከእርሱም ጋር የእስራኤል ልጆች ማህበር ኹሉ በቃሉ ይውጡ፤ በቃሉም ይግቡ። ሙሴም እግዚአብሔር እንዳዘዘው አደረገ፤ ኢያሱንም ወስዶ በካህኑ በአልዓዛርና በማኅበሩ ኹሉ ፊት አቆመው፤ እግዚአብሔርም በሙሴ እንደ ተናገረ፤ ሙሴ እጁን በላዩ (በኢያሱ ራስ ላይ) ጫነበት፤ አዘዘውም>> (ዘኁል.27፣ 19-23)።

በዚህ ዓይነት ኢያሱ በሙሴ ተሾሞ፤ እንደ ሙሴ ኹሉ፤ መስፍን እስራኤልና ነቢየ እስራኤል ኾነ። እስራኤልን በመጠበቅ፣ በማስወጣትና፣ በማስገበት፣ በመመገብና በመንከባከብ ረገድ ኢያሱ እጅግ የታወቀና የተመሰገነ መስፍንና ነቢይ ኾነ።

በዘመነ ሐዲስም ቅዱሳን ሐዋርያት ከጌታችን የተቀበሉትን ሥልጣነ ክህነት ተከታዮቻቸውም እጅ እየጫኑ ይሾሟቸው እንደ ነበር ቅዱስ መጻሐፍ ያረጋግጣል (የሐዋ.6፣ 6፤ 1ኛጢሞ.4፣ 14፤ ዕብ.1፣ 1-3)።

አንብሮተ እድ (እጅ መጫን) የሥልጣነ ክህነት መስጫ ምልክት ከመሆኑም በላይ፤ በረከት (ቡራኬ) ይሰጥበት፣ ፈውስ ይደረግበት ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶን ለመባረክ ወደ እርሱ የመጡትን ሕፃናት እጁን ጭኖ ይባርካቸው ነበር (ማር.10፣ 16)። ጌታችን በልዩ ልዩ በሽተኞች ላይ እጁን በመዘርጋት ወይም በመጫን ይፈውሳቸው ነበር (ማቴ.8፣ 1-4፤ ማቴ.4፣ 41)።

## አንድ ዲያቆን ኾኖ ከመሾሙ በፊት ሊያሟላው የሚገባው መመዘኛ ምንድን ነው?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ባዘዘው መሠረት፣ ሥልጣነ ዲቁና መቀበል የሚፈልጉ ሰዎች፦

ሀ. ጭምቶች
ለ. በኹለት ቃል የማይናገሩ ማለትም ቃላቸው አንድ የኾነ
ሐ. የማይሰክሩ (ከስካር የራቁ)
መ. ነውር የሚያስከትለውን ረብ የማይወዱ ማለትም ነውር የሌለባቸው
ሠ. ንጹህ በልብ የሃይማኖትን ሚስጢር የሚጠብቁ፤
ረ. በቂ ትምህርት ያላቸው መሆን ይገባቸዋል (1ጢሞ.3፣ 810)። እንዲሁም አንድ ሰው በምንኩስና ጸንቶ ማዕርገ ዲቁና በመቀበል ሊያገለግል ይችላል።

## ቅስናስ ለመቀበል የሚያስችል መመዘኛስ ምንድን ነው?

ሥልጣነ ቅስናን (ሥልጣነ ክህነትን) ለመቀበል የሚፈልግ ሰው፦

ሀ. የማይነቀፍ ማለትም ነውርና ነቀፋ የሌለበት
ለ. የአንዲት ሴት ባል
ሐ. የሰውን ፊት አይቶ የማያዳላ
መ. ራሱን የሚገዛ
ሠ. የሚሰብክና በእውነት የሚገስጽ
ረ. እንግዳ ተቀባይ፤
ሰ. ከስካር የራቀና ገንዘብን የማይወድ (ፍቅረ ንዋይ የሌለበት)፤
ሸ. በትምህርቱና በእምነቱ ነቀፋ የሌለበት መሆን ይገባዋል (1ኛጢሞ.3፣15)

በተጨማሪም በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሥርዓት መሠረት ቅስናን ለመቀበል የሚፈልግ ሰው፣ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች መፈጸም የሚገባው ከመሆኑም በላይ ድንግሊቱን በሕግ ያገባ መሆን አለበት። ባልዋ የሞተባትን፣ ወይም የተፈታችውን፣ ወይም ጋለሞታይቱን ያገባ ሥልጣነ ክህነት መቀበል አይገባውም (ዘሌዋ.21፣ 13)። በሥርዓተ ምንኩስናው ጸንቶ ለመኖር የሚፈልግ መነኩሴ ማዕርገ ቅስና ተቀብሎ ማገልገል ይችላል።

## ኤጲስ ቆጶስ መሆን ለሚፈልግ መመዘኛው ምንድን ነው?

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ባዘዘው መሠረት ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ፣ ኤጲስ ቆጶስ የእግዚአብሔር መልክተኛ ነውና፦

ሀ. የማይነቀፍ፤
ለ. የማይከራ፤
ሐ. የማይቆጣና፣ የማይሰክር፣
መ. የማይጨቃጨቅ፣ ነውረኛ ረብን የማይወድ፣

ሠ. ጠንቃቃ፣ ጻድቅ፣ ቅድስና ራሱን የሚገዛ መሆን አለበት፤
ረ. ሕይወት የሚገኝበትን ትምህርት ማስተማር የሚችል፣ በሃይማኖት ትምህርት የበሰለና በድንግልና ጸንቶ የመነኰሰ መሆን ይገባዋል (ቲቶ1፣ 7-10) ግእዙን፣ በተጨማሪም ፍትሐ መንፈሳዊ አንቀጽ 5 እስከ መጨረሻው ያለውን ይመልከቱ።

## ታላቅ ምክር

<<ካህኑ፣ የሠራዊት ጌታ የእግዚአብሔር መልክተኛ ነውና፣ ከከንፈሮቹ (ከአንደበቱ) ዕውቀትን ይጠብቁ ዘንድ ይገባቸዋል፤ ሰዎችም ሕግን ከአፉ ይፈልጉ ዘንድ ይገባቸዋል>> (ሚል.2፣ 7)።

ከትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት 1991 ዓ.ም.
አቡነ ገብርኤል ከጻፉት የተወሰደ።